# የካቲት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የባሻይ ኣውዓሎም ሓረጎት ሓወልት ሲመረቅ የማሕበር ንሓድሽ ልምዓት ቦርድ ሊቀ መንበር ኢ/ር ጥላሁን ውብነህ ያደረጉት ንግግር

ክቡር አቶ ስብሃት ነጋ
የኢፌደሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኣባልና
የኢህአዴግ ምክር ቤት ኣባል

ክቡር አቶ ሙሉጌታ ዓለምሰገድ
በሚኒስትር መዓርግ የኢፌደሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ኣማካሪ

ክቡራን የክልል ተወካዮች

ክቡራንና ክቡራት እንግዶች

በማሕበር ንሓድሽ ልምዓት ስምና በራሴ ስም ዛሬ በሚካሄደው ታሪካዊ የሓወልት ምርቃት በመገኘታችሁ ልባዊ ምስጋናችንን እየገለጽኩ እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ::

ዛሬ የሚከበረው የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ኩራት ብቻ ሳይሆን፣ የጥቁር ሕዝብም መመኪያ ነው:: ብዙ መስዋዕት ከፍለው ያንን ታሪካዊ ድል ላስገኙልንና ነፃነታችንን ላስከበሩልን ከሁሉም ብሔር ብሐረሰቦች የተውጣጡ ቆራጥ ጀግኖች ኣባቶቻችንና ኣያቶቻችን ሁሌም እያመሰገንን በኩራት እናስታውሳቸዋለን::

ከጠላት ጋር መጀመሪያ ኣምባላጄ ላይ፣ ቀጥሎም እንዳየሱስ ላይ፣ በመጨረሻም ዓድዋ ላይ በተደረጉት ውጊያዎች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጎን ተሰልፎ የትግራይ ሕዝብ በጀግንነት ከመዋጋቱ በተጨማሪ ከ100,000 በላይ ለነበረው ዘማች በመመገቡና በመንከባከቡ ውለታውን በማስታወስ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

ኣባቶቻችንና ኣያቶቻችን ተባብረው የውጭ ጠላትን እንዳሸነፉት፣ እኛም ተባብረን ጠላቶቻችንን ድምጥማጣቸውን ማጥፋት ኣለብን:: ጊዜ ሳንሰጥ ጠላቶቻችንን ለማሸነፍ ታጥቀን መነሳት ብሄራዊ ግዴታችን መሆኑን እንመንበት:: የምንገጥማቸው ጠላቶቻችን ሶስት ናቸው:: እነሱም ድህነት፣ HIV/AIDS እና ሙስና ናቸው:: ሙስና የልማት ካንሰር እየሆነ ስለመጣ፣ ሕዝቡን እያሳመመው ነው:: ስለሆነም ሙሰኞችን መቅጣት በተመለከተ የቻይናንና የቬትናምን ተመክሮ መመርመር የሚጠቅም ይመስለናል::

መንግሥት ብዙ የልማት ሥራዎች ኣከናውኗል:: ኣሁንም የኢትዮጵያን ልማት በቀለጠፈና በሰፊው እያፋጠነው ይገኛል::

መንግሥት የሚያካሄደውን የልማት እንቅስቃሴ መደገፍና በልማቱ መሳተፍ ብሄራዊ ግዴታችን መሆኑን በመገንዘብ፣ ማሕበር ንሓድሽ ልምዓት የሚባል መንግሥታዊ ያልሆነ ኣገር በቀል ድርጅት (NGO) ተቋቁሞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል::

ማሕበር ንሓድሽ ልምዓት በዓድዋ ከተማና ኣካባቢው የሚካሄደውን የልማት እንቅስቃሴ በገንዘብ በማተርያል በምክር ይረዳል::

ማሕበር ንሓድሽ ልምዓት ስድስት ዓላማዎች ሲኖሩት፣ ከስድስቱ ዓላማዎች ኣንዱ የዓድዋ ከተማና ኣካባቢው ስልጣኔ፣ ታሪክ፣ ባህል እና ቅርስ እንዲጠበቅና የበለጠ እንዲታወቅ ለማድረግና ዓድዋና ኣካባቢው የቱሪስት መስህብ እንዲሆኑ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል::

ስለሆነም፣ ከምንኮራበት ከዓድዋ ድል ጋር በተያያዘ፣ ለድሉ መገኘት ወሳኝ ሚና ለተጫወቱት ኣገር ወዳድ ኣርበኛ ለባሻይ ኣውዓሎም ሓረጎት መታሰቢያ ሓወልት ማሕበር ንሓድሽ ልምዓት ኣሠርቶ ዛሬ ያስመርቃል::

ባሻይ ኣውዓሎም ከኣባታቸው ከአቶ ሓረጎት ሠረቀብርሃን እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ሳህሉ ባህሩ እንትጮ ኣካባቢ ትኩዝ መኸረም በተባለ ቦታ ተወለዱ::

ባሻይ ኣውዓሎም ጥሩ ጠባይ የነበራቸው፣ ሰው ኣክባሪ፣ የትም ቦታ ከሰው ጋር ተግባቢ፣ ቀልደኛ፣ ተወዳጅ ነበሩ:: ከሁሉም በላይ ተናግረው የማሳመንና ነገርን ኣመዛዝኖ ተስማሚ መፍትሔ የማግኘት ልዩ ችሎታ ነበራቸው::

ከዓድዋ ጦርነት በፊት፣ መተማና ኩዓቲት ላይ ተዋግተዋል:: ራስ ኣሉላ ኣስመራን ቆርቁረው ኣስመራ ሁነው በሚገዙበት ጊዜ፣ ሶስት ፈረንጆች መሓንዲሶች ነን ብለው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ:: የፈረንጆቹን ማንነት ለማረጋገጥ ወደ ምጽዋ ከተላኩት ሰላዮች ኣንዱ ባሻይ ኣውዓሎም ነበሩ:: ፈረንጆቹ መሓንዲሶች ሳይሆኑ ባለሌላ መዓርግ ሰላይ ወታደሮች ሆነው ስለተገኙ እንዲታሰሩ ተደርጓል::

ኢጣልያ የዓድዋን ጦርነት ለመጀመር በምትዘጋጅበት ገዜ፣ ጠላት መሓል ገብተው የሱ ታማኝ ሰላይ በመምሰል ጠላትን ለማሳመን ልዩ ችሎታ ኣላቸው ተብለው ባሻይ ኣውዓሎም በራስ ኣሉላ ተመረጡ::

ባሻይ ኣውዓሎምም የተጣለባቸውን ኣደራ በኣግባቡ እየተወጡ የጠላት ታማኝ ሰላይ ለመሆን በቁ:: የጠላት ጦር ኣዛዥ ጀኔራል ባራቲሪም ያምናቸው ነበር:: ባሻይ ኣውዓሎምም እስልያለሁ እያሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደሰፈሩበት ይሄዱና የጠላት ሁናቴ ምን እንደሚመስል ለራስ ኣሉላ በምስጢር ይነግሩዋቸው ነበር::

ጠላት ጠንካራ ምሽግ ሰርቶ የኢትዮጵያ ሰራዊት ምሽጉ ድረስ መጥቶ እንዲወጋው በተስፋ ይጠብቅ ነበር። ጠላት በቂ ስንቅና ትጥቅ ነበረው።

በኣንጻሩ የኢትዮጵያ ሰራዊት የስንቅ እጥረት ነበረበት። በበሽታም እየተጠቃ ነበር። ስለሆነም፣ ኣፄ ምኒሊክ ሁለት ኣማራጮች ነበሩዋቸው።

ኣንደኛው ኣማራጭ በስንቅ እጥረትና በበሽታ ምክንያት ሳይዋጉ ወደ ኋላ ማፈግፈግ። ሁለተኛው ኣማራጭ ደግሞ ያለው ስንቅ ሳያልቅ፣ ቶሎ ብሎ ጠላት ወደ መሸገበት ሂዶ መዋጋት። ኣፄ ምኒሊክ ሁለተኛውን ኣማራጭ ማለትም ጠላት ወደ መሸገበት ሂዶ መዋጋትን መረጡ።

ሁለቱም ኣማራጮች ለኢትዮጵያ የማይበጁ ነበሩ። ኣፄ ምኒሊክ በእንደዚህ ዓይነት ኣጣብቂኝ እያሉ፣ ባሻይ ኣውዓሎም የዓድዋ ድል እንዲገኝ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል።

ባሻይ ኣውዓሎም፣ ከኢጣልያ ጋር ኣብረው ኢትዮጵያን ሲወጉ የነበሩትን ራስ ስብሓትንና ደጃዝማች ሓጎስ ተፈሪን ከጣልያን ተነጥለው ከኢትዮጵያ ሰራዊት ጋር እንዲቀላቀሉና ከወገኖቻቸው ጎን ሆነው ጠላትን እንዲወጉ ስለኣሳመኑዋቸው፣ ሁለቱም ከነተከታዮቻቸው ወደ ኢትዮጵያ ሰራዊት ተቀላቀሉ።

ሁለቱም የጠላትን ሁናቴ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ አፄ ምኒሊክ ያወጡት የውጊያ ዕቅድ እንዲለወጥ ኣደረጉ። የኣፄ ምኒሊክ ጠላት ምሽግ ድረስ ሂዶ የመዋጋት ዕቅድ፣ እልቂትና ሽንፈት ሊያስከትል የሚችል መሆኑን ለንጉሱ በማስረዳት፣ ጠላት ከምሽጉ እስኪወጣ ድረስ መጠባበቅ ግድ እንደሚልና ጠላትን ለማሸነፍም የበለጠ ታክቲክ መሆኑን በማሳመን ጠላት ምሽግ ድረስ ሂዶ የመዋጋት እቅድ እንዲቀር ንጉሱ ተስማሙ።

ጠላትን ከምሽጉ ለማውጣት ምን መደረግ እንዳለበት ውይይት ሲደረግ፣ ባሻይ ኣውዓሎም ጠላትን ከምሽጉ ሊያወጡት እንደሚችሉ ኣረጋገጡ።

እንዳሉትም፣ ባሻይ ኣውዓሎም ሆን ብለው የተዛባ ኢንፎርሜሽን ለጠላት ጦር ኣዛዥ ለጀኔራል ባራቲየሪ ሰጥተው የጠላት ጦር ከምሽጉ እንዲወጣ ኣድርገዋል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሰራዊት ወደኣለበት ልምራህ በማለትም ጠላት ወደሚፈልገው ቦታ ሳይሆን፣ ሆን ብለው በማሳሳት ጠላትን ወደ ሌላ ቦታ ወሰዱት። ያቦታ የተመረጠው ኣስቀድመው ከራስ ኣሉላ በምስጢር በተስማሙበት መሰረት ነው። ራስ ኣሉላም ምርጥ ወታደሮቻቸው እዚያው ቦታ እንዲጠባበቁ ኣድርገው ስለነበር፣ ጠላት ሲደርስ ኣደጋ ጣሉበት። እዚያው ውጊያው ሲቀጥል ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች የተውጣጣው ተጨማሪ የኢትዮጵያ ሰራዊት ደርሶ ጠላትን በጀግንነትና በማያዳግም ሁናቴ ኣሸነፈው።

ባሻይ ኣውዓሎም ራስ ስብሓትንና ደጃዝማች ሓጎስ ተፈሪን ከጠላት ነጥለው ወደ ኢትዮጵያ ሰራዊት እንዲቀላቀል በማድረጋቸው፣ በረቀቀ ዘዴ ጠላትን ከምሽጉ ለማስወጣት በመቻላቸው፣ ጠላትን ወደሚጠቃበትና ወደሚሸነፍበት ቦታ በማድረሳቸው፣ የዓድዋ ጦርነት ውጤት ከመሸነፍ ኣዝማሚያ ወደ ማሸነፍ በመለወጥ ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ጠብቃ ድል እንድትቀዳጅ በተደረገው የብሔር ብሔረሰቦች ታሪካዊና የጀግንነት ጦርነት ላይ ባሻይ ኣውዓሎም ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል::

የምንኮራበት የዓድዋ ድል ከተገኘ 112 ዓመታት ኣልፈዋል:: በየጊዜው መሠረተ ድንጋይ ይጣላሉ:: ነገር ግን ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ጀግንነትና መስዋእትነት የተገኘው የዓድዋ ድል መታሰቢያ የሚሆን ሓወልት እስከ ዛሬ ድረስ ኣልተሰራም::

በዓድዋው ጦርነት ባሻይ ኣውዓሎም ወሳኝ ሚና መጫወታቸውን በመገንዘብ፣ ከ58 ዓመት በፊት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለባሻይ ኣውዓሎም ብቻ መታሰቢያ የሚሆን እዚህ ስፍራ ኣንድ ድንጋይ ኣኑሯል:: ድንጋዩ ኣሁንም እዚሁ ኣለ:: ድንጋዩ ላይ የነበረው ጽሑፍ ኣሁን ባይኖርም፣ የሚከተለው ተጽፎ ነበር::

> አውዓሎም ሓረጎት::
> አንተ ብትሞት ስምህ ህያው ሆኖ ይኖራል::
> ቀ.ኃ.ሥ.
> ን.ነ.ዘኢ.ት.
> የካቲት 2 ቀን 1942 ዓ.ም.

ማሕበር ንሓድሽ ልምዓት፣ ዛሬ የሚመረቀውን የኣገር ወዳዱና የጀግናው የባሻይ ኣውዓሎም ሓወልት ለማሰራት እድል በማግኘቱ ታላቅ ክብር፣ ኩራትና ደስታ የተሰማው መሆኑን በኣክብሮት ለመግለጽ እወዳለሁ::

ይህንን ሃወልት ለማሰራት ለተባበሩን ሁሉ በማሕበር ንሓድሽ ልምኣት ቦርድ ስምና በራሴ ስም ልባዊ ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ::

ድህነት፣ HIV/AIDS እና ሙስና ከኣገራችን ይጥፉ::

ሞስጋና ለሰማዕታት::

የኢትዮጵያ ነፃነት ለዘለዓለም ይኑር::

# <u>የባሻይ ኣውዓሎም ሓወልቶች</u>

1. በማሕበር ንሓድሽ ልምዓት ተሰርቶ 23/6/2000 የተመረቀው






2. ቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ 23/6/42 ዓ.ም.